የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ
ሪፐብሊክ
የፌደሬሽን ምክር ቤት

The House of Federation
of
The Federal Democratic Republic
of Ethiopia

ቁጥር ፌዐም/ጉ፥/5/303
No
ቀን 23/02/2011
Date

ለወ/ሮ ቦጋለች አሰፋ

<u>ባሉበት</u>

ጉዳዩ፡- <u>የምክር ቤቱን ውሳኔ ስለማሳወቅ</u>

እርስዎ የሕገ መንግስት ትርጉም አቤቱታ ለፌደራል ሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ማቅረብዎ ይታወቃል፡፡

በመሆኑም የፌዴሬሽን ምክር ቤት መስከረም 29 ቀን 2011 ዓ.ም በ5ኛ የፓርላማ ዘመን 4ኛ ዓመት 1ኛ መደበኛ ጉባዔ ባቀረቡት የሕገ መንግስት ትርጉም አቤቱታ ላይ ከፌደራል ሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ የቀረበውን የውሳኔ ሃሳብ ከተመለከተ በኋላ ጉዳዩ የሕገ መንግስት ትርጉም የሚያስፈልገው አይደለም በማለት የሰጠውን የውሳኔ ግልባጭ 4/አራት/ ገጽ ከዚህ መሸኛ ደብዳቤ ጋር አባሪ በማድረግ ሰጥተንዎታል፡፡

ከሰላምታ ጋር

ኬሪያ ኢብራሂም አብ
የፌደሬሽን ም/ቤት አፈ-ጉባኤ

<u>ግልባጭ</u>

- ለፌደራል ሕገ መንግስት ጉደዳዮች አጣሪ ጉባኤ
  <u>አዲስ አበባ</u>
- ለሕገ መንግስት ትርጉም እና የማንነት ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት
  <u>በፌዴሬሽን ምክር ቤት</u>

# የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት 5ኛ የፓርላማ ዘመን

# 4ኛ ዓመት 1ኛ መደበኛ ጉባዔ

**መስከረም 29 ቀን 2011 ዓ.ም**

አመልካች፡- ወ/ሮ ቦጋለች  አሰፋ

ተጠሪ፡- አቶ ስሜ ነጋሽ

**የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ፌዴሬሽን ምክር ቤት አመልካች ያቀረቡትን የሕገ መንግስት ትርጉም ጥያቄ መርምሮ የሚከተለውን ሕገ መንግስታዊ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡**

**<u>ውሳኔ</u>**

ጉዳዩ የተጀመረው  አመልካችና ተጠሪ በጋብቻ አብረው ከቆዩ በኂላ ጋብቻቸው በፍቺ ስለፈረሰ የአሁን አመልካች የንብረት ክፍፍል ጥያቄን ለሲናና ወረዳ ፍ/ቤት በማቅረባቸው ሲሆን  ለዚህ አቤቱታ መነሻ የሆነው በሮቤ ከተማ በደንሳ ጨፌ ቀበሌ ውስጥ 200 ካ.ሜ ቦታ ላይ የሚገኝ ቤት በ10/11/2003 ዓ.ም በተደረገው የጋብቻ ውል የጋራ ንብረት እንዲሆን የተዋዋልን ስለሆነ ተጠሪ ሊያካፍሉኝ ይገባል በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ ተጠሪም ቀርበው ንብረቱን ከጋብቻ በፊት ያፈራሁት ስለሆነ አመልካች መብት የላቸውም በማለት ተከራክረዋል፡፡

ፍ/ቤቱም ግራቀኙን ካከራከረ በኂላ ለአቤቱታው መነሻ የሆነው ቤት ከጋብቻ በፊት ተጠሪ ያፈሩት ቢሆንም ተጠሪ የጋብቻቸው ስነስርዓት በተፈጸመበት ቀን ማለትም በ10/11/2003 ዓ.ም አሁን ክርክር ያስነሳውን ቤት የጋራቸው እንዲሆን ተስማምተው የፈረሙ መሆኑን በቀረቡት የሰውና የጽሑፍ ማስረጃ አረጋግጫለሁ በማለት ቤቱ የጋራቸው ስለሆነ እኩል ይካፈሉ ሲል ወስኗል፡፡

የአሁን ተጠሪም ለባሌ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤትና ለኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ደቡብ ቋሚ ችሎት በየደረጃው ይግባኝ ቢጠይቁም የወረዳውን ፍ/ቤት ውሳኔ አጽንቷል፡፡ ተጠሪ በውሳኔው ቅር በመሰኘት ለኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ ሰበር ሰሚ ችሎቱም ግራ ቀኙን ካከራከረ በኂላ ክርክር ያስነሳው ቤት የተሰራው በ1996 ዓ.ም ሲሆን አመልካችና ተጠሪ የተጋቡት በ9/12/2000 ዓ.ም መሆኑን ከማዘጋጃ ቤት የቀረበው ማስረጃ